ቁጥር OFAGF-03.16/3/33
ቀን 22/06/2015

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ለክብርት ወ/ሮ አለምፀሐይ ጳውሎስ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ኃላፊና
የካቢኔ ጉዳዮች ሚኒስትር
ለክቡር አቶ ምትኩ ዴሬሳ
በሚኒስትር ዴኤታ ማዕረግ
የቤተመንግሥት አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>የቤተመንግሥት አስተዳደር የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤትና አስተያየትን ይመለከታል</u>

በርዕሱ የተጠቀሰውን የቤተመንግሥት አስተዳደር የኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 17 ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና 25 ገጽ የሂሣብ ሪፖርቶች በድምሩ 42 ገጽ የያዘ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እየገለጽን ለኦዲት ግኝቶች የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት እንድትልኩልን እናሳስባለን፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

ከማክበር ሠላምታ ጋር

ጌታሁን ደምጤ
የፋይናንስና ኮምኒኬሽን መ/ቤቶች
ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
Office of the Federal Auditor General

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የቤተመንግሥት አስተዳደር
የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ
የኦዲት ሪፖርት

የካቲት/2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የቤተመንግሥት አስተዳደር

የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ

ኦዲት ሪፖርት

የቤተመንግሥት አስተዳደር የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የቤተመንግሥት አስተዳደር ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አግባብ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡ ኦዲታችን ፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል።

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የቤተመንግሥት አስተዳደር ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው:: ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የቤተመንግሥት አስተዳደር የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል።

ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች(Basic of Audit Opinion)፣

የቤተመንግሥት አስተዳደር የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

1. በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የቀን ሰራተኞችን በኮንትራት ሠራተኛነት በመቅጠር የተፈመ ክፍያ፣

ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ህዳር 18 ቀን 2005 ዓ.ም በቁጥር መ80-839/1 በተፃፈ ደብዳቤ ዘላቂነት ባለውና በተመደበ የሥራ መደብ ላይ በኮንትራት (በጊዜያዊነት) በፌዴራል የመንግሥት መ/ቤቶች ተቀጥረው ያልተቋረጠ አገልግሎት ሲሰጡ የቆዩ ሠራተኞች በቋሚነት እንዲመደቡ፣ በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ባልተመደበና ዘላቂነት በሌለው የሥራ መደብ ላይ በኮንትራት /በጊዜያዊነት/ ተቀጥረው የነበሩ ሠራተኞች ቅጥር እንዲቋረጥ ሆኖ በአስቸኳይ መሰናበት እንዳለባቸው፣ ይህ መመሪያ ለአንድ ጊዜ አፈፃፀም ብቻ የሚያገለግል ሲሆን ከየካቲት 30/2005 ዓ.ም በኋላ ተግባራዊ ማድረግ እንደማይቻል ይገልፃል፡፡ ሆኖም እጅግ አስፈላጊ ከሆነ ለአጭር ጊዜ ብቻ የኮንትራት/ጊዜያዊ ቅጥር መፈጸም አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ ጥያቄው በመጀመሪያ ለሲቪል ሠርቪስ ሚኒስቴር ቀርቦ ተቀባይነት ማግኘት እንዳለበት መመሪያ መተላለፉ ይታወቃል፡፡ በተጨማሪም የፌዴራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁ.1064/2012 አንቀፅ 2 ጊዜያዊ ሠራተኛ ማለት በመንግስት መ/ቤት ውስጥ የዘላቂነት ባህሪይ በሌለው ወይም ሁኔታዎች ሲያስገድዱ በቋሚ የሥራ መደብ ላይ ለጊዜያዊነት ተቀጥሮ የሚሰራ ሰው ነው፡፡ ሆኖም በቀን ሂሳብ እየተከፈላቸው የሚሠሩ የቀን ሰራተኞችን አይጨምርም ይላል፡፡ አስተዳደሩ የሚፈጸመው የዕድገትና የቅጥር ሁኔታ ተገቢነቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

በቤተመንግስት አስተዳደር የወንዶ ገነት ሪዞርት ሆቴል በተለያዩ ቀናት ለቀን ሰራተኞች ክፍያ የክፍያ በቀን 80፣ 100፣ 120 እና 160 ተመን ከመመሪያ ውጭ በኮንትራት ቅጥር በመፈጸም በድምሩ ብር 629,540.00 ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

2. <u>ህጋዊ ባልሆነ ደረሰኝ (በተራ ፋክቱር) የተወራረደ ወጪ በመሆኑ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሳብ፣</u>

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት ስለመንግስት ገንዘብ ክፍያ የመደበኛ ስራ ማስኬጃ ወጪዎች ሲፈፀሙ መሟላት አለባቸው ብሎ ከዘረዘራቸው ውስጥ በቁጥር 4 ላይ ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጪዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መሟላት አለባቸው ይላል እንዲሁም የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ነሀሴ 2001 ዓ.ም ስለደረሰኝ አያያዝ፣ አጠባበቅና ቁጥጥር ባወጣው መመሪያ ቁጥር 28/2001 አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ የሽያጭ ደረሰኝ ቢያንስ የግብር ከፋዩን ሙሉ ስም፣ አድራሻ እና የተመዘገበ የንግድ ስም፣ የገዢውን ሙሉ ስም አድራሻና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ ተከታታይ የሆነ የደረሰኝ ቁጥር እና ሌሎችም መረጃዎችን መያዝ እንዳለበት ይገልጻል::

ይሁን እንጂ አስተዳደሩ ለወጪዎች የተሟላ ትክክለኛ የወጪ ሰነድ በማቅረብ የተወራረደ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፣

- በዋናዉ መ/ቤት በቀን 12/07/2014፣ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 23693፣ ሂሳብ መደብ 2311101 ብር 22,000.00 ከሱራ ፈርኒቸር ሼልፍ እና አበባ ማስቀመጫ ግዥ እና በቀን 6/07/2014 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 529655 በሂሳብ መደብ ብር 17,100.00 ለሆቴል አገልግሎት የሚውል የምግብ ዘይት ህጋዊ ባልሆነ ደረሰኝ (በተራ በፋክቱር) የተወራረደ መሆኑ፣
- በወንዶ ገንት ሪዞርት ሆቴል በብር 362,295.00 ግዥ የተፈፀመ ሲሆን ለተከፈለው ክፍያ ህጋዊ ባልሆነ ደረሰኝ የተወራረደ መሆኑ፣

በድምር ብር 401,295.00 ህጋዊ ባልሆነ ደረሰኝ/ በተራ ፋክቱር/ ሂሳቡ የተወራረደ በመሆኑ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አልተቻለም::

3. <u>ያላግባብ የተከፈለ የቅጣት ሂሳብ፣</u>

የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 ክፍል 2 ተራ ቁጥር 6/1 የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች በኃላፊነታቸው ስር የሚገኘው የመንግስት ሃብት ለተገቢ እና አግባብ ባለው የመንግስት አካል ለፀደቀ ዓላማ ብቻ መዋሉን እንዲሁም አጠቃቀሙ ቁጠባን ብቃትን እና ውጤታማነትን በከፍተኛ

ደረጃ ሊያስገኝ በሚችል መንገድ መፈጸሙን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው ይላል:: አስተዳደሩ በአዋጁ መሠረት ክፍያ የፈጸመ መሆኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ለዓመታዊ የተሽከርካሪ ምርመራ ምዝገባና ተለጣፊ ምልክት መክፈል የነበረበትን በወቅቱ ባለመክፈሉ ምክንያት በድምር ብር 61,800.00 ቅጣት ክፍያ በመፈጸም መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ የዳረገ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

4. <u>በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ክፍያ በተመለከተ፣</u>

የፌዴራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ሁለት የመደበኛና ካፒታል የስራ ማስኬጃ ወጭዎች ሲፈጸም ወጪው ለሚደረግበት ተግባር በበጀት ዓመቱ የተያዘ ወይም ወጪውን ለመሸፈን ቀሪ በጀት መኖሩን እና ወጪው በመስሪያ ቤቱ ዕቅድ ውስጥ የተያዘና በጥሬ ገንዘብ ፍላጎት ላይ የተካተተ መሆኑ ሳይረጋገጥ ወጪ መፈጸም እንደማይገባ መመሪያው ይገልጻል፡፡ አስተዳደሩ ክፍያዎችን በወቅቱ እየፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ወጪዎች ናሙና ኦዲት ሲደረግ፡-

አስተዳደሩ በቀን 30/10/2014 የወጪ ማስመስከርያ ቁጥር 00026145 በሂሳብ መደብ 2111201 ብር 72,000.00 ለአቶ ምትኩ ደሬሳ የቤት አበል ከህዳር 1 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ እስከ የካቲት 30/2013 ዓ.ም ያለዉ የ4 ወር (ብር 72,000.00 =(18,000.00*4)) በ2013 በጀት ዓመት መከፈል ሲገባው እና በተከፋይ ሂሳብ ሳይመዘገብ ከበጀት ዓመት ዉጪ በ2014 በጀት ዓመት ክፍያ መፈፀሙ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

5. <u>ከመመሪያ ውጭ ለቀን ሰራተኞች ድጎማ በሚል የተፈጸመ ክፍያ፣</u>

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 2 አንቀፅ 9 መሰረት ማንኛውም ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ለክፍያዎች መሟላት ያለባቸው ማስረጃዎች መሟላታቸውን እና ስለክፍያው ትክክለኛነት ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግ ይገልፃል፡፡ አስተዳደሩ በመመሪያው መሰረት እያከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ የደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ወጪዎች ናሙና ተወስዶ ኦዲት ሲደረግ፡-

ቤተመንግስት ውስጥ ያሉትን ቅርሶችና ንብረቶች ወደ ተዘጋጀላቸው የማከማቻ ቦታ የማጓጓዙ ስራ ለሚሰሩ 23 የቀን ሰራተኞች ማበረታቻ እያንዳንዳቸው አምስት

ሊትር ዘይትና አስር አስር ኪሎ ዱቄት በድጎማ መልክ እንዲሰጣቸዉ በቀን 08/08/2014 በተጠየቀውና በተወሰነው መሰረት ድጎማው የተደረገ ቢሆንም፡-

- የአስተዳደሩ ኃላፊዎች ከመመሪያ ውጭ ለቀን ሰራተኞች ድጋፍና ድጎማ እንዲደረግ ያለአግባብ የወሰኑ መሆኑ፣
- የአስተዳደሩ ኃለፊዎች ለቀን ሰራተኞች እንዲሰጣቸው ከተፈቀደው ዘይትና ዱቄት ውጭ የተለያዩ የምግብ ግብዓቶችን ከአሰፋሽ ገ/ሚካኤል ግዥ በማከናወን በቀን 29/09/2014 የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 25130 በሂሳብ መደብ 2221103 ብር 80,854.34 ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት ታዉቋል::

6. <u>አገልግሎት ለማይሰጡ ስልኮች የተከፈለ ወጪ፣</u>

የፌዴራል መንግሥት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 አንቀፅ 14 የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ቀረፃ በተራ ቁጥር 2 ላይ በመስሪያ ቤቱ የሥራ እንቅስቃሴ ወቅት ተለይተው የታወቁ ስጋቶችን ለማስቀረት እያንዳንዱ የመ/ቤት የስራ ክፍል አንድን ሥራ ለመፈፀም ሥራው የሚያልፈበትን እያንዳንዱን ደረጃ በመዳሰስ ለሥራው ተስማሚና ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት እንዲቀረፅ ማድረግ እንዳለባቸው ተመለክቷል፡፡ የቤተ መንግስት አስተዳደር የስልክ ክፍያ ወጪ ሂሳብን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

አስተዳደሩ አገልግሎት የማይሰጡ 26 የቀጥታ ስልክ መስመሮች ማዘጋት ሲገባው ባለማዘጋቱ ለመስመር ኪራይ በየወሩ ለእያንዳንዳቸዉ ብር 16.52 በመክፍል በበጀት ዓመቱ በድምር ብር 5,154.24 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

7. <u>በስህተት የተመዘገበ የተከፋይ ሂሳብ፣</u>

የፌደራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 5 በንዑስ አንቀጽ ሀ ማናቸውም ክፍያ የሚፈጸምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለው አካል ሲፈቀድ ብቻ በተከፋይ ሂሳብ መያዝ እንዳለበት እንዲሁም አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 5/ሐ የተለያዩ አካላት ቀንሰው ያስቀሩትን የግብር እና ሌሎች ሂሳቦች ለሚመለከተው ግብር አስገቢ አካል ወቅቱን ጠብቀው ማስተላለፍ እንዳለበት ያስቀምጣል፡፡ የአገልግሎት መ/ቤቱ መሰረት

የተከፋይ ሂሳቦችን ለመከታተል ተገቢው የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋቱንና ተከፋይ ሂሣቦችን በገባው ግዴታ መሰረት በወቅቱ የሚከፍል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በሰኔ 30/2014 ዓ.ም በሂሳብ ሪፖርት ከሚታየው ውስጥ፡-

- በሂሳብ መደብ 6171101(ልዩ ልዩ ተከፋዮች) በድምሩ ብር 3,455,476.75 (ከአንድ እስከ አምስት ዓመት) በኢፍሚስ ምዝገባ በወቅት በስህተት የተመዘገበ ሲሆን እንዲስተካከል በየዓመቱ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም አሁንም የምዝገባ ማስተካከያ ያልተደረገ መሆኑን በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እና 7 ከተመለከቱት ሁኔታዎች በስተቀር የቤተመንግሥት አስተዳደር የ2014 በጀት ዓመት የሂሳብ ሪፖርት በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ መሰረት የተፈጸመ በመሆኑ እንዲሁም የሂሳብ ሪፖርቶቹ በሂሳብ አያያዝ ማእቀፍ መሰረት የተዘጋጁ በመሆናቸው በእኛ አስተያየት አጥጋቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል።

<u>ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች(Emphasis matter)፣</u>

1. <u>የዕቃ ገቢ ደረሰኝ ሞዴል 19 ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ፣</u>

   በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል አንድ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ዕቃው ወደ መ/ቤቱ ዕቃ መጋዘን ለመግባቱ የዕቃ ገቢ ደረሰኝ መቅረቡ ማረጋገጥ እንዳለበት ተገልጿል፡፡ የቤተመንግስት አስተዳደር በመመሪያው መሰረት ትክክለኛነት መሆኑን ለማረጋገጥ የወጪ ሂሳቦች በናሙና ኦዲት ሲደረግ፣

- በቀን 27/04/2014 የወጪ ማስመከሪያ ቁጥር 00022193 የሂሳብ መደብ 2231102 ከእዮብ አፈወርቅ የመጋረጃና የሶፋ ስራና የመጋረጃ ግዥ ብር 384,999.30 እና
- በቀን18/8/2014 የወጪ ማስመከሪያ ቁጥር 00024626 አሽንዳ 28 ጌጅ ግዥ የተፈጸመ ብር 89,258.40፣

ድምር 474,257.70 ብር ለሶፋ ስራ፣ የመጋረጃ እና የአሽንዳ 28 ጌጅ ግዥ ክፍያ ተፈጸመ ቢሆንም ንብረቱ ወደ ንብረት ክፍል መግባቱን የሚያረጋግጥ የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ በመሆኑ ክፍያው በገባው ልክ እንደተፈጸመ ትክክለኝነቱን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

2. <u>ያለሂሳብ መደቡ/አርዕስቱ ሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ ወጪ፣</u>

የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ዓ.ም. በክፍል ሁለት አንቀፅ 6 ተራ ቁጥር 4 ላይ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በበጀት አደረጃጀት ሥርዓት መሠረት የተፈቀደላቸው በጀትና የወጣውን ወጪ በሚያሳይ መልኩ ተለይቶ በተሰጠ የበጀት መለያ መደብ ተጠቅመው የሂሳብ እንቅስቃሴያቸውን መመዝገብ እንዳለባቸው መመሪያው ይገልጻል የቤተመንግስት አስተዳደር የወጪ ሂሳቦችን በትክክለኛው የሂሳብ አርዕስታቸው እየመዘገበ መሆኑን ለማረጋገጥ የወጪ ሂሳቦች ናሙና ተወስዶ ኦዲት ሲደረግ፡- በድምሩ ብር 624,574.03 ያለ ሂሳብ አርዕስቱ በሌላ የሂሳብ መደብ/አርዕስት የተመዘገበ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

3. <u>ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት</u>

የፌደራል መንግስት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሶስት አንቀፅ 12 ተራ ቁጥር 1 ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት ለበጀት አመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛና የካፒታል በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠር እንዳለበት ይገልጻል፡፡ አስተዳደሩ የበጀት አጠቃቀሙን በመመሪያው መሰረት እያከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲቻል በ2014 በጀት ዓመት አስተዳደሩ ከተፈቀደው በጀት ውስጥ የመደበኛ በጀት በየፕሮግራሙ ከ10% (በመቶ) በላይ ያልተሰራበት በጀት መኖሩን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በ2014 በጀት ዓመት ለየአርዕስቱ ከተደለደለው በጀት የመደበኛ በጀት የብር 53,536,387.36 እና የካፒታል ብር 282,870,641.58 በድምሩ ብር 336,407,028.74 ስራ ላይ ያልዋለ በጀት መኖሩ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

4. <u>በወቅቱ ያልተጠናቀቁ ግንባታዎች በተመለከተ፣</u>

የፌዴራል መንግስት ሰኔ/2002 ባወጣው የግዢ አፈፃፀም መመሪያ ክፍል 7 አንቀጽ 28 ቁጥር ንዑስ ቁጥር 1 የመንግስት መ/ቤቶች የተለየ ሁኔታዎች ካላጋጠሙ በስተቀር ከአቅራቢዎች/ከስራ ተቋራጮች/ ጋር የተደረገውን የውል ስምምነቶች በፍጥነት ተፈጻሚ ማድረግ እንደሚገባቸው በተጨማሪም በፌደራል መንግስት የግዢ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 16/27/3 ሸ አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን፣ የምክር አገልግሎቱን የግንባታ ዘርፍ ሥራውን ወይም አገልግሎቱን አጠናቆ ባያስረክብ ላዘገየበት ጊዜ የሚወሰደውን እርምጃ በተመለከተ በመመሪያው ተራ ቁጥር 16/27/4/ሀ - ሐ አቅራቢው ሳይፈጽም በቀረው የውሉ መጠን ላይ በየቀኑ 1% ወይም 1/1000 የጉዳት ካሳ እንደሚከፍል በዚህ ዓይነት የሚታሰበው መቀጫ የውሉን ዋጋ 10% የሚበልጥ መሆን እንደሌለበት፣ ለውሉ አፈጻጸም መዘግየት በሥራው እንቅስቃሴ ላይ የበለጠ ችግር የሚያስከትል ከሆነ የመንግሥት መ/ቤቱ የመቀጫው መጠን 10% እስኪሞላ ድረስ ለመጠበቅ ሳይገደድ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን መሰረዝ እንደሚችል ይገልጻል፡፡

ይሁን እንጂ አስተዳደሩ የግንባታና መሰረተ ልማት ስራዎችን በመመሪያውና በውሉ መሰረት ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በእድሳትና በግንባታ ላይ የሚገኙ፡-

- የቤተመንግሥት አስተዳደር ቢሮ ግንባታ፣
- የቤዛዊት ቤተ መንግስት እድሳትና አዲስ የህንፃ ግንባታ ፕሮጀክት፣
- የቤተመንግሥት አስተዳደር ኪችን እና ላውንደሪ፣

በውሉ መሰረት መጠናቀቅ ካለባቸው ጊዜ በተጨማሪ ከ 209 - 1835 ቀናት የዘገዩ ከመሆኑ በተጨማሪ የስራ አፈጻጸማቸው ከ60.61% እስከ 96.85% ድረስ በመሆኑና በወቅቱ ባለመጠናቀቁ እንዲሁም በቀረው ገንዘብ ላይ ላዘገዩበት

የጉዳት ካሳ ብር 179,106,789.60 መክፈል ሲገባቸው ያልተቀጡ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)፣

1. የቋሚና አላቂ ንብረት አያያዝን በተመለከተ፣

በመንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 በአንቀፅ 65 በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ክፍል2 አንቀጽ 6 ረ መሰረት አስተዳደሩ የንብረት ቆጠራ አድርጎ ቆጠራው ከንብረት መዝገብ ጋር እንዲመሳከር የሚደረግና ከወጪ ቀሪው የሚረጋገጥ መሆኑን፣ እንዲሁም የመንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት አስተዳደሩ የንብረት አያያዝ፣አጠቃቀምና አስተዳድር ተገቢው ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በዋናው መ/ቤት

- ብዛት ያላቸው የተለያዩ ቅርሶች በመጋዘን ውስጥ ተከማችተው የተገኙና ከቧንቧ መለዋወጫ እቃዎች ጋር በአንድ ላይ የተቀመጡ መሆኑ፣
- ብዛት ያላቸው የተለያዩ ንብረቶች ያለአግባብ ከተሽከርካሪዎች ጋር በመጋዘን ውስጥ ተከማችተው የተገኙ መሆኑ፣
- አስተዳደሩ ግቢ ውስጥ ብዛት ያላቸው የተለያዩ ማሽኖች፣ ቆርቆሮ እና የተለያዩ ንብረቶች ያለ አግባብ በየቦታው ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፣
- በአስተዳደሩ ውስጥ የሚገኙ እጅግ ውድና በዋጋ ሊተመኑ የማይችሉ ታሪካዊ ቅርሶችን በንብረት ቆጠራ ያልተካተተ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል።

የወንዶ ገነት ሪዞርት ሆቴል

የዕቃ ግምጃ ቤት የአሰራር ክፍተቶች

ቋሚ እና አላቂ እቃዎች በንብረት ግምጃ ቤት (Store) ውስጥ በአንድ ላይ ተቀምጠው መገኘታቸው፣

የዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች

የልብስ ማድረቂያ ማሽን የማይሰራ ብዛት 1፣ ቴሌቪዝን ብዛት 5፣ ኮሚፒተር ከነማዘር ቦርድ ብዛት 1፣ የቪድዮ ካስት ማጠንጠኛ ብዛት 1፣ ቴፕ የሙዚቃ

ማጫወቻ ብዛት 1፣ ስታፕላይዘር ብዛት 1፣ ድቪ ድፕለየር ብዛት 1፣ ቴፕ ድቪድ ማጫወዎቻ ብዛት 1፣ ቴፕ ካስት ማጫወቻ ብዛት 2፣ ፕርንቴር ብዛት 4፣እስፕከር ትናንሽ ብዛት 2 ፣ የዲሽ ተቀባይ ብዛት 3፣ ታይፕራይተር ብዛት 2፣ የጎማ ቼርኬ ብዛት 1፣ የመኪና ወንበር ማጌጫ ብዛት 13፣ የሳር ማጭድ ብዛት 4፣ የሽንት ቤት መቀመጫ ሰሀን ብዛት 21፣ ፍርጂ ባለ አንድ ብዛት 1፣ የቡና ማሽን ብዛት 1፣ የመጸዳጃ መቀመጫ ክዳን ብዛት 18 ፤የሽንኩር መላጫ ማሽን ብዛት 1፣ የእጅ መታጠቢያ ሳሀን ብዛት 17፣ የመጸዳጃ ቤት ውሀ ማጠራቀሚያ ብዛት 21፣ ሻውር ትሪ ብዛት 18፣ የእጅ መታተቢያ ሳሀን ተሸካሚ ብዛት 15፣ ሳምሰግ ቴፕ ብዛት 1፣ የተለያዩ ብዛታቸው 24 የሆኑ የመኪና ጎማዎች፣ አምቦ ውሃ ባዶ ሳጥን ብዛት 88፣ ትልቁ ባለ 25 ሊተር ጀሪካን ብዛት 330፣ ቢራ ሳጥን 342፣ ለስላሳ ሳጥን 55፣ አሮጌ ባለሽቦ ባለ 1ሜት አልጋ ብዛት 2፣ አሮጌ ድንኳን ትልቅ ብዛት 5፣ አሮጌ አልጋ ልብስ ብዛት 27፣ ነጭ መገራጀ አሮጌ ብዛት 16፣ አሮጌ ወፍራም መጋራጀ ብዛት 31፣ ትራስ ጨርቅ ብዛት 395፣ አሮጌ አንሶላ በነጠላ ብዛት 185፣ አሮጌ ትራስ ብዛት 7፣ አሮጌ ትንሹ ድንኳን ብዛት 20፣ አሮጌ ምንጠፍ ብዛት 2፣ 1.20 አሮጌ አልጋ ብዛት 3፣ ፍራሽ በላ 1ሜትር ብዛት 1፣ ኪሎ ሚዘን 1፣ Gas) ኤሌክትሪክ እስቶብ ብዛት1፣ መፈልፈፈያ ማሽን ብዛት 2፣ ማሽን ብዛት 1፣ ፍርጅ ማሻን ብዛት 2፣ ፍርጅ ብዛት 1፣ መጭመቂያ ማሽን ብዛት 2፣ ሳር ማጨጃ ማሽን ብዛት 4፣ በንብረት ክፍል ተከማችተው ያለ አገልግሎት የሚገኙ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

2. <u>የተሽከርካሪዎች አያያዝና አጠባበቅ በተመለከተ፣</u>

የፌዴራል መንግስት የንበረት አስተዳደር መመሪያ ቀጥር 9/2003 ዓ.ም አንቀጽ 5 የመመሪያዉ አላማ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በእጃቸዉ ያለውን የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፤ የመጠቀም፣ መቆጣጠርና አገልግሎት ለይ በሚያውሉበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ ማስወገድ እንዳለበት ያዛል፡፡በዚሁ መመሪያ መሰረት የአስተዳደሩ ተሽከርካሪዎች በጥንቃቄ

የሚያዙ፤የሚጠቀሙባቸው እና በመቆጣጠር አገልግሎት የሚሰጡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በአስረተዳደሩ ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገኙ ተሸከርካሪዎች ያለ መጠለያ በየቦታው ዛፍ ስር ቆመው የሚገኙና ለብልሽት በሚዳርግ መልኩ ፀሐይና ዝናብ እየተፈራረቀባቸው የሚገኝ መሆኑ፤
- 117 ሊብሬ የሌላቸው ተሸከርካሪዎች መኖራቸው
- ሞዴላቸው ሮዊ 750 FL2.5V ከሆኑት ተሸከርካሪዎች ውስጥ በሳምፕል ለማየት እንደተሞከረው የሰሌዳ ቁጥር ቢ.መ 202 4-18293፣ ቢ.መ 223 4-18408፣ ቢ.መ 164 4-18412፣ ቢ.መ 179 4-18346፣ ቢ.መ 162 4-18335፣ ቢ.መ 207 4-17209፣ ቢ.መ 177 4-18415፣ ቢ.መ 211 4-18409፣ ቢ.መ 183 4-18771፣ ቢ.መ 245 4-17047፣ ቢ.መ 233 4-17041 የሞተር ቁጥራቸው ተለጣፊ ሆኖ የተገኘ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

3. <u>የገቢ ዕቅድ በዝርዝር ያልተዘጋጀ ስለመሆኑ፣</u>

የፌዴራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 አንቀጽ 6 ተራ ቁጥር 1 የመንግሥት መ/ቤቶች የዓመቱን የገቢ እቅድ በወር ከፋፍሎ ማዘጋጀት እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡

ይሁን እንጂ ወንዶ ገነት ሪዞርት ሆቴል በመመሪያው መሠረት የገቢ እቅድ በዝርዝር በየሂሳብ መደቡ የማያዘጋጅና ያልፀደቀ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

4. <u>የሚሰበሰብ ገቢ በየ እለቱ ወደ ባንክ ገቢ የማይደረግ ስለመሆኑ፣</u>

የፌደራል መንግስት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 አንቀፅ 8 በፊደል ሠ መሰረት የሰነዶች አጠቃቀምና አጠባበቅ የአሰራር ስርአት እንዲሁም የሚመለከታቸው ሀላፊዎች የተዘረጋው ቁጥጥር የሚሰራ መሆኑን ማረጋገጥ የሚችልበትን የቁጥጥር ስልት መዘርጋት እንዳለበት ተመለክቷል፡፡ ይሁን እንጂ፡-

ከፈረስ ኪራይ አገልግሎት ለክለብ አባልነት፣ ከፈረስ ኪራይ አገልግሎት ለሌሎች ደንበኞች፣ ከጋጣ ኪራይ አገልግሎት፣ ከሠረገላ አገልግሎት፣ ከፍግ ሽያጭ፣ ከናይለን ገመድ ሽየጭ፣ በግቢ ውስጥ ለልደት ለሠርግና መሰል ፕሮግራሞች

በቡድን ለመዝናናት፣ ከከሰል ሽያጭ እና ለማገዶ የሚሆን ደረቅ እንጨት ሽያጭ፣ የተሰበሰበ ገቢ በየእለቱ ወደ ባንክ ገቢ የማይደረግ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

የህግ ጉዳዮች በተመለከተ(Compliance Issue)፣

1. **ባለጸደቀ መመሪያ የተሰበሰበ ገቢ በተመለከተ፡፡**

   የሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር190/2002 ስለ ፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር ክፍል 4.21.1 የመንግስት መ/ቤቶች ለሚያቀርቡት አገልግሎት አዲስ ተመን ወይም በነባር ዋጋ ላይ የሚደረግን ለውጥ በሚመለከት ያላቸውን የውሳኔ ሃሳብ በሚኒስትሩ በኩል ለሚኒስቴሮች ም/ቤት አቅርበው ማጽደቅ እንደሚኖርባቸው የተገለጸ ቢሆንም አስተዳደሩ፡-

   በቤተመንግስት አስተዳደር የወንዶ ገነት ሪዞርት ሆቴል የፍል ውሃ አገልግሎት፣ የመኝታ፣ የምግብ እና የመጠጥ አገልግሎት በበጀት ዓመቱ ብር 17,516,555.30 የተሰበሰበ ቢሆንም በመመሪያው መሰረት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርቦ በማፀደቅ ገቢውን መሰብሰብ ሲገባው ባልጸደቀ የአገልግሎት ክፍያ ገቢ እየሰበሰበ ሲሆን በ2013 በጀት ዓመት ተመሳሳይ የኦዲት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም እስካሁን ያልተስተካከለ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

2. **ከተፈቀደው በላይ በካዝና የተገኘ ጥሬ ገንዘብን በተመለከተ፣**

   የቤተ መንግስት አስተዳደር የባንክና የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር ሂደት በፌደራል መንግስት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁ.6/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 7 ተራ ቁጥር 5(ሐ) መሰረት የባንክና ጥሬ ገንዘብ በሳጥን እንዲያድር (በፒቲ ካሽ) እንዲያዝ በአስተዳደሩ ከተወሰነው የገንዘብ መጠን በላይ በካዝና ቢገኝ ሰራተኛው በህግ ተጠያቂ እንዲሆን የማድረግ ኃላፊነት እንዳለበት ይገልጻል፡፡ አስተዳደሩ ከብር 300,000.00 በላይ በካዝና እንዲያድር በሚያደርግ ሰራተኛ ላይ የህግ አግባብ በሚፈቅደው መሰረት እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

   በበጀት መዝጊያ ወቅት በውስጥ ኦዲተሮች በተደረገ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ላይ በዋና ገንዘብ ያዥ ወ/ሮ ገነት ፍሰሐ ብር 314,917.62፣ በረዳት ገንዘብ ያዥ አቶ አበባው ተስፋ ብር 358,170.59 እና በረዳት ገንዘብ ያዥ አቶ ደረሰ

መንገሻ 400,000.00 በካዝና ተገኝቶ የተቆጠረ ሲሆን በብልጫ በድምሩ ብር 173,088.21 በካዝና እንዲቀመጥ የተደረገ መሆኑ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

3. <u>የእጅ በእጅ ሽያጪ ደረሰኝ የተወራረደ ሂሳብ፣</u>

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት ስለመንግስት ገንዘብ ክፍያ የመደበኛ ስራ ማስኬጃ ወጪዎች ሲፈፀሙ መሟላት አለባቸው ብሎ ከዘረዘራቸው ውስጥ በቁጥር 4 ላይ ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጪዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መሟላት አለባቸው ይላል፡፡ አስተዳደሩ የሚያወጣቸው ወጪዎች የተፈጸሙት በተሟላ ሰነድ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፡-

በአስተዳሩ በበጀት ዓመቱ በድምሩ ብር 6,445,867.68 ገንዘቡን ስለመቀበሉ ህጋዊ የሆነ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ (ካሽ ሬጅስተር ደረሰኝ) በመቀበል ክፍያ መፈጸም ሲገባው በካሽ ሬጅስተር ማሽኑ ላይ የተፈጠረውን ችግር ከሚመለከተው አካል ሳይገለጽ፣ ፍቃድ ሳያቀርብ፣ ምክንያቱ ሳይታወቅና ሳይፈቀድ በእጅ በእጅ የሽያጪ ደረሰኝ ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ ከመሆኑ በተጨማሪ የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ በገቢዎች ሚኒስቴር ማህተም ያልተመታበት መሆኑን በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

4. <u>በውሉ ቀነ ገደብ እቃው ገቢ ባለመሆኑ ያልተቀነሰ የጉዳት ካሳ ቅጣት፣</u>

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 16.26 ውል መፈረም ንዑስ አንቀጽ 16.27.4 በንዑስ አንቀጽ 16.27.3 መሰረት (ሸ) አቅራቢው በውሉ በተመከለተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን ማስረክብ (ሀ) አቅራቢው ሳይፈፅም በቀረው የውል መጠን ላይ በየቀኑ 1% ወይም 1/1000 የጉዳት ካሳ መክፈል እንዳለበት ይገልፃል፣ ነገር ግን (ለ) የውሉን 10% መበለጥ እንዳሌለበት በግልፅ ተቀምጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አስተዳደሩ በ2014 በጀት አመት ለትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ጋር ውል በመዋዋል የተለያዩ ዕቃዎችን አቅራቢወች እንደሚያቀርቡ ይታወቃል፡፡ አስተዳደሩ አቅራቢዎች ውል ከገቡበት ቀን ጀምሮ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ዕቃውን ወደ አስተዳደሩ መጋዘን ክፍል ገቢ ባለማድረጋቸው አቅረቢዎቹ ላሳለፉቸው ቀናት የውሉን

1/1000ኛ ባዘገዩበት ቀናት ቀንሶ የሚያስቀር መሆኑን ለማረጋገጥ የግዥ ወጪዎች ናሙና ተወስዶ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በቀን 25/06/2014፣ ኢንቮይስ ቁጥር 23266፣ ሂሳብ መደብ 2231107 እና ብር 2,362,905.00 የተለያዩ ብዛት ያላቸው የመኪና ዕቃዎች ለማቅረብ ውል ገብቶ አቅራቢው በውሉ መሰረት እንዲያቀርብ የውል ስምምነት ቢፈርምም በወቅቱ ገቢ ባለማድረጉ ሃያ ሶስት(23) ቀናት በመዘግየቱ በውሉ መሰረት ሳይፈፀም በቀረው ብር 2,362,905.00 ውስጥ ብር 54,346.82 የጉዳት ካሳ ቅጣት ሳይቀረጥ የተገኘ መሆኑ፣
- በቀን 29/10/2014፣ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 00026178፣ ሂሳብ መደብ 2311101 እና ብር 1,672,285.15 የተለያዩ የመስተንግዶ ግዥዎች ከኦሚዳድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ጋር ውል ገብቶ በውሉ መሰረት እንዲያቀርብ የውል ስምምነት ቢፈርምም በወቅቱ ገቢ ባለማድረጉ በአስራ ዘጠኝ (19) ቀናት በመዘግየቱ ብር 31,773.42 የጉዳት ካሳ ቅጣት ሳይቀረጥ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑን፣

በድምሩ ብር 86,120.24 ንብረቱን በውሉ መሰረት በወቅቱ ገቢ ባለማድረጋቸው አቅረቢዎቹ የውሉን 1/1000ኛ ባዘገዩበት ቀናት የጉዳት ካሳ ቅጣት ሳይቀረጥ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑን በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

5. <u>ያለውድድር ቀጥታ የተከናወነ ግዥ፣</u>

በፌዴራል መንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 51 ንኡስ አንቀጽ 1/ሀ የመንግስት መ/ቤቶች ከአንድ አቅራቢ ግዥ መፈጸም የሚችሉት እቃው ወይም አገልግሎቱ የሚገኘው ከአንድ እጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ እንደሆነ፤ እንዲሁም በፌደራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ/2002 ክፍል 5 አንቀፅ 24 ተራ ቁጥር 24.1 የመንግስት መ/ቤቶች አስቀድሞ ማቀድ እስከተቻለ ድረስ ግዥን በግልፅ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈፀም እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡

ይሁን እንጂ በቤተመንግስት አስተዳደር የወንዶ ገነት ሪዞርት ሆቴል የጽዳት ሳሙና ግዥ በድምር ብር 891,941.90 ከመመሪያ ውጪ ያለውድድር በቀጥታ ግዥ በማከናወን ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

6. በጨረታ መገዛት ሲገባው በመከፋፈል በዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ ግዥ፣

በፌዴራል መንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 33 ቁጥር 4 በዚህ አዋጅ ወይም በግዥ መመሪያው የተዘረጉ የግዥ ስርዓቶችን ለማሻሻል የመንግስት መ/ቤቶች በአንድነት መፈጸም የሚገባቸውን የእቃ፤ የግንባታ ወይም የአገልግሎት ግዥዎችን መከፋፈል የለባቸውም ይላል፡፡ ይሁን እንጂ አስተዳደሩ፡-

- በዋናዉ መ/ቤት ብር 516,028.00 የጥገና አገልግሎት ግዥ እና
- በወንዶ ገነት ሪዞርት ሆቴል ብር 794,609.00

በድምሩ ብር 1,310,637.00 አስቀድሞ ማቀድ እስከተቻለ ድረስ በአንድ ላይ ሊፈጸሙ የሚገባቸውን የእቃና የአገልግሎት ግዥዎችን በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈጸም ሲገባ በመከፋፈል በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ የተገዙ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

7. መመሪያ ከሚፈቅደው የብር መጠን በላይ የተፈፀሙ የለቀማ ግዥ፣

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ 2002 ዓ.ም አንቀጽ 24/1፣አንቀጽ 24.3 ፊደል ሀ እና ለ፣ አንቀጽ 24.12 እንደ ቅደም ተከተላቸው፡የመንግስት መ/ቤቶች አስቀድሞ ማቀድ እስከተቻለ ድረስ ግዥን በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው፡፡ በተጨማሪ የገንዘብ ሚኒስቴር መስከረም 25, 2014 ዓ.ም በተሻሻለው የግዥ መመሪያ ተራ ቁጥር አንድ ላይ የጥቃቅን ግዥዎች (እቅድ ውስጥ ያልተካተቱ) ለአንድ ጊዜ ግዥ ብር 10,000.00 በዓመት ከ150,000.00 ብር ያልበለጡ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን በቀጥታ ግዥ ከማናቸውም ሻጭ ድርጅት መፈጸም እንደሚችሉ ተገልጿል፡፡ አስተዳደሩ በዚህ መመሪያ መሠረት ግዥ የሚፈፅም መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፣

በቤተመንግስት አስተዳደር በወንዶ ገነት ሪዞርት ሆቴል በበጀት ዓመቱ በድምሩ 1,532,337.02 ብር በቀጥታ ለተፈጸሙ ጥቃቅን ግዥዎች ክፍያ የፈጸመ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

8. <u>በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ፣</u>

በፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳር አዋጅ ቁጥር 648/2001፣ በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 የተሰብሳቢ ሂሳብ በአንቀጽ 8 ቁጥር 4 ከፊደል ሀ-ሰ በዝርዝር በተቀመጠው መሰረት በወቅቱ እየተሰበሰበ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በ2014 በጀት ዓመት በሂሳብ ሪፖርት ላይ በተሰብሳቢ ሂሳብ ከሚታየው ውስጥ፡-

- በሂሳብ መደብ 5217109 ብር 54,410.56 ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት የቆየ መሆኑ፣
- በሂሳብ መደብ 5217110 (ለሰራተኞች ቅድሚያ ክፍያ) ብር 22,213.73 ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት የቆየ መሆኑ፣
- በሂሳብ መደብ 5217205 (4253) (ለእቃ አቅራቢዎች የሚፈጸም ቅድሚያ ክፍያ) ብር 744,242.94 ከአንድ አመት በላይ ሳይወራረድ የቆየ መሆኑ፤
- በሂሳብ መደብ 5217301 (ልዩ ልዩ ቅድሚያ ክፍያዎች) ብር 25,025.00 ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት የቆየ መሆኑ፣
- በሂሳብ መደብ 5217399 (ሌሎች ተሰብሳቢ) ብር 8,288,000.00 ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት እና ብር 210,031.50 ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ሳይወራረድ የቆየ መሆኑ፣

በድምሩ ብር 9,343,923.73 በወቅቱ ያልተወራረደ ውዝፍ በተሰብሳቢ ሂሳብ የሚታይ መሆኑን በኦዲት ስራ ወቅት ለማወቅ ተችሏዋል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት